# ቃለ አባይ

*ከተዘራ አሰጉ / ከምድረ እንግሊዝ/*

የአባይ ውሎ ቋጠሮ
ለዘመናት ተወድሮ ተጥለፍልፎ ።

የውሉ መፍቻ ተሰውሮ
መለስ ብሎ የሚይዋዛው አጥቶ ።

አባይ የተፈጥሮ ልግስናው ዳጉሶ
ያለኛ ፈቃድ ማን-ነክቶት ተብሎ ።

የአያቶቻችን የአትዮጵያ ፈተና
በአባይ የደረሰባቸው ጉንተላ ።

የሰከነ ማስተዋሉ ትዕግስቱ ጣራ ነክቶ
በንካፈል የዋህነት ህሳቦተ ካባ ተጎንፎ ።

ኢትዮጵያየም በነገረ ስራቸው ተደመመች
የትዕግስትን መራራነት አጤነች ።

የፍሬዋን ጣፋጭነት አሰላች
በይሁነ ህሳቤ ነገሩን ቺላ አለች ።

የአባይ ዳር ዳሩ ወስጠ ውብቱ
ቅላፄ ድምፁ የፏፏቴው ህብሩ ።

በመረዋ ድምፃቸው
አዋፋት አባይን አወደሱ ።

የተፈጥሮ ዙሪያ ገቡ
ተፋሰስ ጅረቱ ለአባይ አረገዱ ።

ውስጠ ይዘቱ የአባይ ማንነቱ
ገዘፈ አጎመራ ኢትዮጵያዊነቱ ።

የዓለም ሊቃያት ለፈፉ
ነገሩ ለዓለም አስረገጡ ።

የአባይ ግዝፈተ ኢትዮጵያዊነቱ
መነሻ ውሉ ምንጩ ፍሰቱ ።

የአባይ ነገረ ስራው ውስጠ ሚስጥሩ
ቸር ለጋስ አያዳሌ መሆኑ ፤

የተፈጥሮ ልግስናውን አንጋራ ባሉ
በንዳዴ በርሃ ሲቆሉ ማየቱ አይበጂም ብለው ባወጁ ፤

ይሄ ሆኖ ሳለ የአብሮ መኖር መነሻ ዉሉ
"አልጠግብ ባይ ሲተፋ ያድራል" እንዲሉ ፤

በቸሯ ኢትዮጵያ በለጋሱ አባይ አደሙ
ጦር ሰበቁ ሞከሩ ምድረ ዉሃውን ሊያደፈርሱ ፤

አይቀጡ ቅጣት ተቀጡ
ተንኮል ደባቸው ገባ ወዳአፎቱ ፤

ይህ እብሪታቸው አላወላትፍ ሲላቸው
የጥምዝምዚት አሴሩ አቡይ ሆነ ልባቸው ፤

ከዕኩያን ጋር ተቀናጂ
አጉራሻቸውን አመሱ ፤

በአጉል ፍራቻ ተወጠሩ
በቢሆንስ አባዜ ደነበሩ ፤

ከዕለት ዕለት በአጉል ሴራ ማድባት ያዙ
አባይና እናቱ ኢትዮጵያየ "ቦ ጊዜ ለኩሉ" አሉ ፤

በራስ ሃብት ፀጋ የበይ ተመልካች መሆኑ
ዉስጠ እግራቸው ተቃጠለ ተከኑ ነደዱ ፤

እምነት ማተባቸውን ሳይፈቱ
በፀሎት በድዋው ለአምላክ ፍርድ አንጋጠጡ ፤

አባይና ኢትዮጵያ ተማከሩ
በጋራ ሰላም ጉዞ  ተማገሩ ፤

አባይም በፏፏቴው ጉሩምራሜ
ህዳሴውን ተቀኘ ቃል ጋባ ለአገሬ ፤

እስከመቼ እናት ምድሬን
በጨለማ አጉሬ አሰመርሬ ፤

እንግዲህ ባርሲኩርሲው አትዳሙ
ተንኮለ አድማ ሴራውን አጢኑ ፤

አባይ ለፈፈ ሰፊው ደረቱን
ሃይል ርዝማኔ ወበቱን ፤

ጀባ አልን እሱነቱን
አርዮ የጉዟችን ዕልም ውሉን ፤

ደጓ ሃገሬና ሕዝቧ ተጋመዱ
የአባይን ሹክታ አዳመጡ ፤

በደቦ አፈፍ አሉ ተነሱ
የዕዳሴውን ብርሃን ሊያበስሩ ፤

አባይና ሃገሬ በይፋ ለፈፉ
የጋራ ተቋዳሽነትን አሰረገጡ ፤

ውጥን ሰራው የወደፊት በረከቱ
ለወል ጥቅም መበጀቱን አሰመሩ ፤

ውሃና አፈሩስ አሉ ሳያፍሩ
በደግነታችን አፌዙ ተዳፈሩ ፤

አባይም ተናደደ ወገሸ ተቆጬ
ፏፏቴውን እያላጋ እንባውን ወደ አምላክ ረጬ ፤

አያዳሌው ሰማ መላእከ ጠሩን ላከ
ቸር ምድሬን የጊዮንን ውሃ ምንጭ ለደፈረ ፤

ነበልባለ ሰይፈ ቅጣቱን አወረደ
እንደፈርሆን ያበጠው ልባቸው ራደ ፤

መለሰ ብሎ አየ አገናዝቦ
የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንክሮ ፤

እጅ ለእጅ ተጋመደ
የባለአደራ ቃሉን አንግበ ፤

አባይ ቃለ ዉል አሽራውን ከተበ
ወይውልፍጭ የእናቴ የኢትዮጵያ ነኝ አለ ፤

አባይ ቃለ ውሉን ላያጥፍ ቃል ከገባ
እኛም የችሮታው ተቋዳሽ ነንና ፤

በሶስት ምህረ ድርጊት ተጋምደን
አባይ ኢትዮጵያ ሕዛባዊነታችን ቀምረን ፤

በመካከላችን ገብቶ ሊያተራምሰን ያሰበን
ያካብተነውን ጌጣዊ ግማደ ወኔ ከታጠቅን ፤

እምየ ኢትዮጵያ አንድ ትብዕል አላት
የራሷን አትሰጥ የሌላም አይሻት ፤

የሚገፋት ጠንቋ ሌላን መግፋት እርሟ
ንብ ከአውራው ይነሳል የነኳት ለትማ ፤

የቲዎድሮስ ፤ የዩሃንስ የአሉላን ዉሎ
የሚኒልክ የሕዝበ ኢትዮጵያ ግድል ተረስቶ ፤

የጠቢበ ቃሉ ራህየ ውለታው ተዘንግቶ
መለስ ተብሎ ሳይወደስ በድፍረት ተደርጉሶ ፤

ታሪክን ደባብሰው ትላንትን ረስተው
ከነካኩንማ ብረታ ብረቱን ቆርቆሮ ተማምነው ፤

እንኳንና ዛሬ እንድ ሆነን ተነስተን
ረቂቅ ሳይንሱን አካተን አንግበን ፤

በጣሙን ያውቁናል ትላንትም አልቻሉን
በጦር በጎራዴ በሽመል ሰንመክት ፤

ሰማኝ የሃግሬ ሕዝብ
ይሰምራል ዕልማችን ፤
አባይ ይገደባል ራዕዩ ይሳካል
የጨልማ ጉዞ ከእንግዲህ ያከትማል ።

*ተዘራ አሰጉ / ከምድረ እንግሊዝ/*